

**የእጩ ስም:-** **Julie Kang (ጁሊ ካንግ)**
**የምርጫ ዘመቻ ስም:-** **Julie for Seattle D5 (ጁሊ ለሲያትል D5)**
**የምርጫ ዘመቻ ድህረ ገጽ፦** **https://julieforseattle.com/**
**የሥራ መደብ፦** **የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት 5**
**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር፦** **206.880.3873**
**የእጩ መተዋወቂያ (የ200 ቃላት ገደብ)፦**

የዲስትሪክት 5 የረጅም ጊዜ ነዋሪ፣ አስተማሪ፣ እና ንቁ የማህበረሰብ አባል ነኝ። በሰሜን ሲያትል ህይወቴን የገነባሁ ስደተኛ እንደመሆኔ መጠን፣ የከተማ ውሳኔዎች የሠራተኛ ቤተሰቦችን፣ ስደተኞችን፣ እና አነስተኛ ንግዶችን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዴት እንደሚቀርጹ ተረድቻለሁ።

መሪዎቻችን እንዲያዳምጡን እና ዲስትሪክታችን በትክክል ምን እንደሚፈልግ እንዲረዱ እንፈልጋለን። ቅድሚያ የምሰጣቸው ነገሮች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት መቻል፣ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት፣ ደህንነት፣ እና ቤት አልባነት እና የስደተኞች ጥበቃዎች ናቸው።

ሙያዊ ሕይወቴን በሕዝብ እና በከፍተኛ ትምህርት አሳልፌያለሁ፣ ባለብዙ ቋንቋ ተማሪዎችን ለመደገፍ መምህራንን አሰልጥኛለሁ። በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሽንግተን እና በሲያትል ዩኒቨርሲቲ ሠርቻለሁ፣ ትላልቅ ፕሮግራሞችን በመምራት እና በመንደፍ፣ ውስብስብ የህዝብ በጀቶችን በማስተዳደር፣ እንዲሁም በተጠያቂነት፣ በፍትሃዊነት፣ እና በውጤቶች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ የዘርፍ ሽርክናዎችን በመገንባት።

በሃለር ሌክ ማህበረሰብ ክለብ ቦርድ ውስጥ አገለግላለሁ፣ በምግብ ባንክ ውስጥ በፈቃደኝነት እሠራለሁ፣ ስደተኞች ማህበረሰባችንን አስተምራለሁ እና ህብረተ-ሰቡን ከ ICE በፊሽካ እና በሌሎሽ ነገሮሽ ለማንቃት እሰራለሁ፣ እና አነስተኛ ንግዶችን ለመደገፍ የFuseD5 የእግር ጉዞዎችን እመራለሁ። የWEA ዩኒየን ኩሩ አባል ነኝ እንዲሁም ባለቤቴ የUFCW 3000 አባል ነው።

ለከተማችን ምክር ቤት የማህበረሰብ እውቀትን፣ የባንክ ልምድን፣ የፖሊሲዎች እውቀትን እና አስተማማኝ አመራርን ይዤ እመጣለሁ። ማህበረሰባችን የሚፈልገው ዓይነት መሪ ለመሆን ቃል እገባለሁ - ድምጽ ለሌላቸው ሰዎች የምታዳምጥና የምትሟገት ሰው።

የእርስዎን ድጋፍ ለማግኘት እና ዲስትሪክታችንን ለመወከል ክብር ይሰማኛል።

*ይህች እጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ ተሳታፊ ናት።*



**የዕጩ ስም:-** Silas James (ሳይለስ ጄምስ)

**የምርጫ ዘመቻ ስም፡-**ሳይለስ ለሲያትል (Silas for Seattle)

**የምርጫ ዘመቻ ድረ ገጽ፡-** https://silasforseattle.com/

**ለከተማው የሚወዳደሩበት የሥራ መደብ፡-** City Council District 5 (የ ዲስትሪክት 5 የከተማ ምክር ቤት)

**የምርጫ ዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** (425) 224-5463

እኔ Silas James እባላለሁ፣ ከተማችን ለሁሉም ሰው በተሻለ ሁኔታ እንድትሠራ ለማድረግ በDistrict 5 የSeattle City Council አባል ለመሆን ዕጩ ሆኜ ቀርቤያለሁ። እንደ አንድ አካል ጉዳተኛ አስተማሪ፣ ተመራማሪ፣ ተሟጋች እና የ Seattle Disability Commission (የሲያትል የአካል ጉዳተኞች ኮሚሽን) ሰብሳቢ፣ በተበላሹት ሥርዓቶቻችን ተስፋ ቆርጫለሁ። ሀብታም ኮርፖሬሽኖች ተገቢውን ድርሻ እንዲከፍሉ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች እንዲስፋፉ፣ እንዲሁም በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ የደህንነትና ለአየር ንብረት ፍትህ የሚረዱ መፍትሄዎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ በቁርጠኝነት እና በትጋት እሰራለሁ። አቅመ ደካማ ለሆኑ ጎረቤቶቻችን የምትመች Seattleን መፍጠር ከቻልን፣ ሁላችንም ተጠቃሚ እንሆናለን። በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ጎረቤቶቻችን የሚሠራ ሲያትል ከፈጠርን ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል።

አብዛኛውን የሕይወት ዘመኔን የመንግሥት ድጋፎችን (Public benefits) በመጠቀም ያሳለፍኩ ሲሆን፣ በዚህም ልምዴ ስለ እነዚህ ውስብስብ ሥርዓቶች ከፍተኛ ክህሎት ያካበትኩ ባለሙያ ሆኛለሁ። ግለሰቦችን በመምራትና ቡድኖችን በማስተማር ስኬታማ እንዲሆኑ ስረዳ የቆየሁ ቢሆንም፣ አሁን ግን ለመላው Seattle የሚተርፍ ጥቅም ለማስገኘት መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥን ለማምጣት ቆርጬ ተነስቻለሁ።

ሰዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስፈልጋቸውን ግብአቶች ለማቅረብ እንዲሁም ማንነታቸው፣ መገኛቸው ወይም ያላቸው የገንዘብ መጠን ሳይለይ ሰፈሮቻችን ለሁሉም ደኅንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆኑ ለማድረግ በዚህ ምርጫ እወዳደራለሁ።

የዲሞክራሲ ቫውቸሮችዎን (Democracy Vouchers) ለSilas for Seattle በመስጠት ለዘመቻዬ ድጋፍ እንዲያደርጉልኝ እጠይቃለሁ። የከተማችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የእኛ እንጂ የቢሊየነር ኮርፖሬሽኖች አለመሆኑን ያረጋግጡ።

*ይህ ዕጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።*



የዕጩ ስም፡- Nilu Jenks (ኒሉ ጄንክስ) የምርጫ

ቅስቀሳው ስም፡- Neighbors for Nilu (ኔበርስ

ፎር ኒሉ)

የምርጫ ቅስቀሳ ድረ-ገጽ፡- https://www.neighborsfornilu.org

የሥራ መደብ፡- City Council District 5 (የሲቲ ካውንስል ዲስትሪክት 5)

የምርጫ ቅስቀሳ ስልክ ቁጥር፡- 206-321-9890

North Seattle (ሰሜን ሲያትል) ልጆቼን እያሳደግኩ ያለሁበት፣ ከጎረቤቶቼ ጋር የቅርብ ወዳጅነት የመሰረትኩበት እና ማህበረሰቡ እንዲጠነክር ለረጅም ጊዜ የደከምኩበት አካባቢ ነው። በውሻ መናፈሻዎች ከሚደረጉ ጭውውቶች ጀምሮ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን እስከመሳተፍ ድረስ ከጎረቤቶች ጋር መገናኘት እና ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበትን ማህበረሰብ መፍጠር ደስ ይለኛል። ለዚህ አካባቢ ካለኝ ፍቅር የተነሳ በዝህ ምርጫ ላይ ዲስትሪክት 5ን ለማገልገል እወዳደራለሁ።

የኢራናውያን ስደተኞች ልጅ፣ የማህበረሰብ ተሟጋች እንዲሁም ሥራ የምትሠራ የሁለት ልጆች እናት ነኝ። ትምህርት ቤቶቻችንን ለማሳደግ፣ ሰፈሮቻችንን ይበልጥ ለማጠናከር እና ሁሉንም የሚያሳትፍ ማህበረሰብ ለመገንባት ከጎረቤቶች ጋር በመሆን ለዓመታት በትጋት ሰርቻለሁ።

በትምህርት ቤቶች፣ በመናፈሻዎች እና በትራንስፖርት አቅራቢያ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች እንዲኖሩ በከተማው ምክር ቤት (City Council) ውስጥ ጠንክሬ እሰራለሁ። በቅርብ ጊዜ በተከሰቱት የግሮሰሪ እና የመድኃኒት ቤቶች መዘጋት ምክንያት በቤተሰቦች እና በአረጋውያን ላይ የደረሰውን የምግብ አቅርቦት ክፍተት ለመቅረፍ መፍትሄ እፈልጋለሁ። ለአየር ንብረት ፍትህ፣ ለተሻሻለ የትራፊክ ደህንነት እና ለበርካታ አስርት ዓመታት ቃል የተገቡልንን የእግረኛ መንገዶች ለመገንባት ቁርጠኛ ነኝ።

በFairVote Washington (ፌርቮት ዋሽንግተን) በነበረኝ ቆይታ፣ ዲሞክራሲያችን ይበልጥ እንዲጠነክርና እንዲጠበቅ የተለያዩ ማህበረሰቦችን በማስተባበር የበኩሌን አስተዋጽኦ አድርጌያለሁ።

ይህ የምርጫ ቅስቀሳ District 5 አብሮን የሚቆም፣ የሚያዳምጥና ውጤት የሚያመጣ አመራር ይገባዋል ብለው በሚያምኑ ጎረቤቶች ጉልበት የሚንቀሳቀስ ነው። እኔም ለማከናወን የወሰንኩት ይህንኑ ነው።

*እኚህ ዕጩ በዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።*



**የእጩ ስም፡-** Dimitri Georgakopoulos (ዲሚትሪ ዮርጋኮፑሎስ)

**የዘመቻ ስም፡-** Passionate Advocacy for a better Seattle (ለተሻለ ሲያትል አጥብቆ መሟገት)

**የሥራ መደብ፡-** የከተማ ምክር ቤት ዲስትሪክት

5

**የዘመቻ ስልክ ቁጥር፡-** 206.409.7275

**የእጩ መተዋወቂያ (የ200 ቃላት ገደብ)፡-**

እኔ ሲያትል ነኝ — እናም የከተማዋ ጠንካራ ተሟጋች ለመሆን ተዘጋጅቻለሁ።

ሞንትሌክ ውስጥ ያደግኩ፣ ጋርፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማርኩ፣ በሲያትል ዩኒቨርሲቲ የተቀረጽኩ — ይህች ከተማ ናት የገነባችኝ። ለሶስት አስርት ዓመታት ያህል እዚህ ሥራ ፈጣሪ ነበርኩ፡- መጀመሪያ የግሪክ ምግብ ቤቶችን ባለቤት በመሆን፣ ከዚያም ፈቃድ ያለው የሪል እስቴት ደላላ በመሆን ሥራዬን በመገንባት። የሲያትል ተስፋዎች ከባድ ፈተናዎች ሲገጥሟቸው እና ውጤታቸውም አሳዛኝ ሲሆን ተመልክቻለሁ።

ፖለቲከኞች ለኑሮ ተመጣጣኝ ዋጋ ቃል ይገባሉ። ሲያትል አሁንም ለኑሮ ውድ ሆና ቀጥላለች። ደህንነትን ቃል ይገባሉ። አውሮራ አሁንም በወሲብ ዝውውር እና በዘራፊ ንግዶች የተሞላች ናት። የብስክሌት መሄጃ መንገዶችን ይገነባሉ፣ ነገር ግን የንግድ ኮሪደሮች ባዶ እየሆኑ ነው፣ ሥራ ፈጣሪዎች ድጋፍ አጥተዋል፣ እና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው መኖሪያ ቤቶች ያለ ፍትሃዊ እኩልነት ወይም ራዕይ በዲስትሪክት 5 ላይ ተከማችተዋል።

እና መሪዎች ትኩረታቸው በተከፋፈለበት ወቅት፣ ዝምተኛ ስጋት እያደገ ነው — አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ሥራዎችን እያጠፋ እና የከተማችንን የእድገት የወደፊት ሁኔታ እየቀየረ ነው።

ዲስትሪክት 5 አስደናቂ ነው — የባህሎች ውህደት፣ አስደናቂ መልክዓ ምድሮች እና እጅግ በጣም ብዙ ያልተነካ አቅም አለው። ይህንን የሚያይ፣ ለዚህ የሚታገል እና በዚህ ላይ እርምጃ የሚወስድ መሪ ይገባዋል።

እኔ የሙያ ፖለቲከኛ አይደለሁም። እኔ ጎረቤትዎ፣ ጠበቃዎ እና እውነታን የምቀበል ሰው ነኝ። ዲስትሪክት 5

እውነተኛ መፍትሄዎች ያስፈልጉታል። እኔ እነሱን ለማቅረብ ዝግጁ ነኝ።

*ይህ ዕጩ የዲሞክራሲ ቫውቸር ፕሮግራም ተሳታፊ ነው።*